# እስከመቸ

## እስከመቸ

ሀ፣ ሁ፣ ሂ ነበረ

የኛ ፊደላችን

በኪነ ጥበብ ደንብ

የተማርን ሁላችን

አዲሱ ጎሰኛ

ያ ይቅርብኝ ብሎ

ማን እነቱን ጥሎ

ይድነቃችሁ ብሎ

ከድብደባ አልፎ መጨፍጨፍ ቀጠለ

አልሳካለት ሲል

አማራን ከትግሪ

አሮሞን ከአማራ

ነጥሎ ነጣጥሎ

ጉራጌን “ከአናሣ” በጥል እንዲተይይ

ተብትቦ ተብትቦ

ይኸ ነው ከንግዲህ

ያንተ አዲሱ ስምህ

እያለ በመሥጠት ለጎሣኛው ሁሉ

እንዲያ ብቻ ሳይሆን እሥ በሱ እንዲባላ

በክልል ወጥሮ

አሥሮ አስቀመጠው በፍርሃት አሸከላ

## እስከመቸ

ጎሣውን ሲያሟክሽ

አለው ንጥረ ወርቁ

በአዕምሮ ብቻ  ሳይሆን

በቁሳቁስ ዘርፎች

ከሁሉ እንዲልቁ

## እስከመቸ

እንዳናወግዘው

የለውም ሃይማኖት

በምን እንታረቅ

ከምሥቅልቅል መንግሥት

አይከለከልም በሪ እንኳን እንዳይበላ

በአውድማ ሲወቃ

ምን አምጡ ብሎ ነው

ይምሥቅልቅል መንግሥት

የኢትዮጵያን ልጆች

መንገድ ሄዱ ብሎ

የሚያቅጥላቸው በጥይት ባዙቃ

## እስከመቸ

እንዳናወግዘው

የለውም ሃይማኖት

በምን እንታረቅ

ከምሥቅልቅል መንግሥት

ኧረ ባላህ በሉ ውይንም በየሱስ

እስከመቸ ድረስ እንዲህ እንታመስ

© ለምለም ፀጋው፣ ታህሳሥ 10፣ 2007

ለሰባዊ መብታቸው በመናገራቸውና በሰልፍ አቢቱታ ስላሰሙ ለተገድሉና ለታሰሩ ሁሉ ከአክብሮት ጋር የተበረከተ